# Voice Of Ethiopian People (VOEP)



## ወደ ኢትዮጵያ ለሚተላለፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ራዲዮ
## የአስተዋጽኦ መርሐግብር በSan Jose

በኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሀን በአገዛዙ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር የሆነበት አስከፊ ሁኔታ ነው ዛሬ ያለው። ይህን ለመለወጥ ይልቁንም ከአምባገነኑ ሥርዓት መዳፍ ለማላቀቅ ያልተቋረጠ ትግልን ይጠይቃል። የኢትዮጵያ ሕዝብ አንደበቱ ሆነው የሚናገሩለት ልሳኑ ሆነው ብሶቱን የሚያሰማበት ነጻ ፕረስ እንደሚያስፈልገው መናገር ማሰልቸት ይሆንብናል። በተለይ በአሁኑ ወቅት የነፃ ፕረስ አባላት ከወህኒ በዋሉበት የሕዝቡ ድምፅ በታፈነበት ሁኔታ አማራጮች መፈጠራቸው ግድ ይሆናል። እውነተኛ የሕዝብ ድምፅ የሚሰማባቸው አውታሮች መኖር ወይም መፈጠር አለጥርጥር ዛሬ የተያያዝነውን ሰላማዊ ትግል ወደፊት የሚገፋ ለውጤትም የሚያበቃ እንደሚሆን አያጠራጥርም።

በዚህ መነሻነት የሕዝብ ድምፅ ይከበር በሚል መሰረታዊ መርህ በመመርኩዝ ነው የአጭር ሞገድ ራዲዮ በሳምንት ሁለት ቀናት ማለትም ማክሰኞና ቅዳሜ ወደ ኢትዮጵያ የሚተላለፍ የተቋቋመው። በዚህም ሕዝባዊ አላማ በመመስረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ራዲዮ መርሀ ግብር ላለፉት አምስት ወራት ሲሰራጭ ቆይቷል። በዚህ ሂደት ውስጥ ዘወትር ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ሙያቸውን በነፃ በመለገስ የፋይናንስ ወጪውን በመሸፈን የበኩላቸውን አከናውነዋል። የሀ የተቀደሰ አስተዋጽኦ ቀጣይነት ይኖረው ዘንድ የሁሉንም ድጋፍ መፈለጉ አልቀረም።

በመጪው April 29, 2006 ዓ.ም. በSan Francisco Bay Area CA የድጋፍ ኮሚቴ አዘጋጅነት የአስተዋጽኦ መርሐግብር ተወጥኗል። “ ሀምሳ ሎሚ ለሀምሳ ሰው ጌጡ” እንዲባል ነውና ሁሉም የድርሻውን እንዲያበረክት ስንጠይቅ በታላቅ አክብሮት ነው።

**ቀኑ** - April 29, 2006
**ቦታ** - 1015 Park Ave San Jose, Ca 95126 (Park Ave እናLincoln Ave መጋጠሚያ)
**ሰዓት** - 04:00PM

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ይከበር!!

e-mail : BayArea@voep.net website: www.voep.net